በጉምሩክ ኮምሽን

የአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

CUSTOMS COMMISSION

ADDIS ABABA KALITI CUSTOMS BRANCH OFFICE

ቁጥር፡ደ/አ/ድ/11/2011

ቀን፡-15/11/2011

ለ: ንግድ ገቢ ዕቃ አወጣጥ የሥራ ሂደት

ለ: ገቢ ሂሳቦች አስተዳደርና የቀረጥ ተመላሽ የሥራ ሂደት

ለ: ተተው የተወረሱ መጋዘን አስተዳደር የሥራ ሂደት

ለ: ወጪ ንግድ ያልሆኑ ገቢ ዕቃዎች የሥራ ሂደት

ለ: ድህረ ዕቃ አወጣጥ የስራ ሂደት

ለ: ኢንተለጀንስና ኮንትሮባንድ የሥራ ሂደት

ለ: ደንበኞች ትምህርት ቡድን

ለ: ጉምሩክ አቤቱታ አጣሪ ጽ/ቤት

ከ፡ ደንበኞች አገልግሎትና ድጋፍ ቡድን

<u>ኢ.አ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት</u>

ጉዳዩ፡- <u>የተሰጠ ውሳኔን ስለማሳወቅ፣</u>

በጉምሩክ አቤቱታ አጣሪ ዳሬክቶሬት በቁጥር 6.4/0039/12 በቀን 15/11/2011 ዓ.ም ስለሺ ስህን ያቀረቡትን አቤቱታ መሰረት በማድረግ በዳይሬክቶሬቱ የተሰጠውን ዉሳኔ ኮፒ አያይዘን በአድራሻ ያሳወቅን በመሆኑ በዚሁ መሰረት አስፈላጊው እንዲፈጸም እናሳስባለን፡፡

ከሰላምታ ጋር

ግልባጭ

ለ፡ ህግ ተገዢነት ም/ሥራ አስኪ.ያጅ

ለ፡ አምራችና ወጪ ዕቃዎች ም/ሥ/አስኪ.ያጅ

ለ፡ ገቢ ዕቃዎች ኦፕሬሽን ም/ሥ/አስኪ.ያጅ

ለ፡ ደንበኞች ትምህርትና ድጋፍ የሥራ ሂደት

<u>ኢ.አ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት</u>

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የጉምሩክ ኮሚሽን
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
CUSTOMS COMMISSION

ቀን 11 ሐምሌ 2012
Date
ቁጥር 6.4/0039/12
Ref.No.

ለስለሺ ስህን /0911259044/

አዲስ አበባ

ጉዳዩ፡- ውሳኔ ማሳወቅን ይመለከታል፤

በ08/04/2011ዓ/ም በተጻፈ ማመልከቻ የአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት በዲ/ዮን ቁጥር፡- C-2557/2012, C-24889/13 አስመዝግበው ወደ ሀገር ውስጥ ያስገቡትን ዕቃ ላይ ያስተላለፈውን የዋጋ ውሳኔ በመቃወም አቤቱታ ማቅረብዎ ይታወቃል።

የአቤቱታው ፍሬ ነገር

የቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት የድህረ እቃ አወጣጥ ኦዲት ቡድን ባደረገውየውስን ኦዲት በዲክለራሲዮን ቁጥር C-2557/12 እና C-24889/13 ለሆቴል ግንባታ የሚውል ፌሮ ብረት በቀረጥ ነፃ ወደ ሀገር ውስጥ ያስገባ ቢሆንም ለሆቴሉ ግንባታው ከሚያስፈልገው መጠን በላይ ስለሆነ ከሚፈለገው የብረት መጠን በላይ ለገባው የአርማታ ብረት የመንግስት ቀረጥና ታክስ ቅጣትን እና ወለድን ጨምሮ እንዲከፍሉ በተወሰነ ውሳኔ ላይ የቀረበ ቅሬታ ነው።

ቅ/ጽ/ቤቱ የሰጠው ምላሽ

በቀረጥ ነፃ የገባው ብረት ግንባታው ከሚያስፈልገው መጠን በላይ ስለሆነ በልዩነት የተገኘውን የአርማታ ብረት ቀረጥና ታክስ ከእነ ቅጣቱ እንዲከፍሉ በማለት ውሳኔ ሰጥቷል።

ዳይሬክቶሬቱ የያዘው ጭብጥ

ቅ/ጽ/ቤቱ ያስተላለፈው የዋጋ ውሳኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚል ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምሯል፡፡

ውሳኔ

ዳይሬክቶሬቱ የቀረበለትን የፅሁፍ ማመልከቻና የተለያዩ የሰነድ ማስረጃዎችን በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀፅ 153 እና በመመሪያ ቁጥር 107/2007 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት መርምሮ የውሳኔ ሀሳብ ካቀረበ በኋላ የጉምሩክ ኮሚሽነር የሚከተለውን ውሳኔ አስተላልፏል። ቅሬታ አቅራቢው በቅሬታቸው ህንፃውን ለማስገንባት በባለሙያ የተጠናና የህንፃውን ቢል ኦፍ ኳንቲቲ በሕጋዊ ባለፈቃድና ባለሙያ የተሰራና የኛ ባለሙያና የኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ባለሙያ በመናበብ በሰነድ የተደገፈ ማጣራት እንዲደረግ አስፈላጊ ሰነዶችን ይዘን ቀርበን በድጋሚ እንደገና እንዲጣራና እንዲታይልን፤ በመስራት ላይ ላለነው ያልተጠናቀቀ ህንፃ ሳይቱ ድረስ ቀርቦ መፈተሽ የሚያስፈልግ በመሆኑ በድጋሚ እንዲታይልን እና እንዲመረመርልን በማለት ቅሬታቸውን አቅርቧል፡፡ ዳይሬክቶሬቱም ባደረገው ማጣራት ቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ለውሳኔ ምንሻ ያደረገው የኮንስትራክሽን ሚኒስቴር በስትራክቸራል ዲዛይን መሰረት ኦዲት በማድረግ ግንባታው ሊወስድ የሚችለው የአርማታ ብረት REINFORCING BAR/ መጠን 485,603.43 ኪ.ግ መሆኑን በቁጥር03.06/0071/01/11 በቀን 18/01/2011 ዓ.ም በፃፈው ደብዳቤ ለቅ/ጽ/ቤቱ ባሳወቀው መሰረት ቅ/ጽ/ቤቱ አመልካችው ወደ ሀገር ያስገባው የአርማታ ብረት መጠኑ 927,489 ኪ.ግ ሲሆን ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሰጠው መረጃ መሰረት በልዩነቱ ላይ ቀረጥና ታክስ ከእነ ቅጣቱ እንዲከፍሉ መወሰኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡ ዳይሬክቶሬቱም የአመልካች ቅሬታ ከቀረበለት በኋላ ለቅሬታ መነሻየሆነው የኮንስትራክሽን ሚኒስቴር መስሪያ ቤት በመሆኑ ዳይሬክቶሬቱ ለከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን በቁጥር 6.4/593/11 በ12/09/2011 ዓ.ም በፃፈው ደብዳቤ በአቤቱታ አቅራቢውና በሚመለከታቸው የመንግስት መስሪያ ቤቶች እጅ የሚገኙ ህጋዊ የዲዛይን ሰነዶችን እንዲሁም የሆቴል ግንባታው ያለበትን ደረጃ በአካል በመመልከትና ከግንባቢ በማስገባት ከዚህ ቀደም የተሰጠው የብረት ፍጆታ ግምት ትክክል ስለመሆኑ አስተያየት እንዲሰጠን ፤ ግምቱ ስህተት ያለበት ከሆነም ለሆቴሉ ግንባታ የዋለው የብረት ግምት ተስተካክሎ ውጤቱ እንዲገለጽልን በማለት በደብዳቤ ጠይቋል፡፡ የሚንስቴር መ/ቤቱ የኮንስትራክሽን ዘርፍ ተወዳዳሪነት ማበልጸጊያ ቢሮ በቁጥር 851መ250/277 በ25/10/2011 ዓ.ም በፃፈው ደብዳቤ ከዚህ በፊት ተቋማችሁ እንድንመረምር የላከልን ዲዛይን በ27/10/2003 ዓ.ም የፀደቀ ዲዛይን ሲሆን ግንባታ ላይ የዋለው ዲዛይን ደግሞ የጸደቀው በ01/12/2004 ዓ.ም መሆኑን ያረጋገጥን ሲሆን ይህ ዲዛይን ደግሞ በህንፃ ከፍታና በመጠን ልዩነት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ለአብነትም የመጀመሪያው የጸደቀው ዲዛይን B1+G+14 ሲሆን በ2004 ዓ.ም ጸድቆ ወደ ስራ የገባው ዲዛይን B2+G+14 ይህ ደግሞ የ1 ቤዝመንት ተጨማሪ ልዩነት ያለው ሲሆን በተጨማሪም መዋቅ በዲዛይኑ የተካተተ ሲሆን በሌላ በኩል ቀድሞ የነበረው የቤዝመንት ዲዛይን 781.425 ካ.ሜ ሲሆን በ2004 ዓ.ም የጸደቀው የቤዝመንት ዲዛይን 1231.56 ካሬ ሜትር እንዲሁም በሌላ በኩል ቀድሞ የነበረው የቤዝመንት ዲዛይን ... /as built/ ... ከግራውንድ እስከ 2ኛ ፎቅ በላይ ያለው የስፋት መጠን 1517.86 ካሬ ሜትር በእያንዳንዱ ወለል ላይ ያለው መሆኑን ... ቀደም ብሎ ለመስሪያ ቤታችን ያቀረባችሁት ዲዛይን እና አሁን ጸድቆ ስራ ላይ በዋለው ዲዛይን የሚፈጀው የብረት መጠን 837,869 ኪ.ግ ብረት የፈጀ መሆኑን

እየገለጽን በግንባታ ቦታው ተገኝተን ባደረግነው ምልከታ በግቢው ውስጥ ተጨማሪ ብረቶች ተከማችቶ ያለ መሆኑን እና ብረቱም ለአጥር ግንባታና ለወንዝ መከላከያ ግንባታ ስራ እንደሚውል ለዚህም ስራ የዲዛይን ስራዎችን ቅሬታ አቅራቢው እያሰሩ መሆናቸውን ገልፆ በደብዳቤ ገልፀውልናል፡፡ ዳይሬክቶሬቱም ከሚኒስቴር መ/ቤቱ የቀረበውን ማስረጃ መሰረት አድርጎ አመልካችሁ የሚያስገነቡትን ግንባታ አካላዊ ጉብኝት ያደረገ ሲሆን ግንባታው ሙሉ ለሙሉ ያልተጠናቀቀ እና የቀሩ ስራዎች እየተሰሩ መሆኑን ማረጋገጥ ችሏል፡፡ በተጨማሪም ሚኒስቴር መ/ቤቱ እንደገለፀው ተራፊ የአርማታ ብረት በግቢ ውስጥ መኖሩን አረጋግጧል፡፡ ስለሆነም አመልካችሁ ወደ ሀገር ውስጥ ያስገባው የአርማታ ብረት 927,489 ኪ.ግ ሲሆን በከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር የኮንስትራክሽን ዘርፍ ተወዳዳሪነት ማበልጸጊያ ቢሮ በባለሙያ ታይቶ ህንፃው የፈጀው የብረት መጠን 837,869 ኪ.ግ የአርማታ ብረት መሆኑን አረጋግጦልናል፡፡ ይህም በግልጽ የሚያመላክተው ቅሬታ አቅራቢው ህንጻውን ገንብቶ ስለጨረሰ ነው ያልተጠቀመው ተራፊ ብረት 89,620 ኪ.ግ የአርማታ ብረት መኖሩን ያሳያል። በሌላ በኩል ለህንጻው ግንባታ የብረት መጠን ፍጆታ ተምኖ የላከልን ተቋም ተራፊ ብረት በህንጻው ቅጥር ግቢ ውስጥ ያለ መሆኑን አሳውቆናል፡፡ በሌላ በኩል ቅሬታ አቅራቢው በአካል ቀርቦ ባስረዱት መሰረት ተራፊው ብረት ለአጥር መስሪያነት እና ለወንዝ መከላከያ አገልግሎት የሚውል ነው በማለት አስረድተዋል፡፡ ይሁን እንጂ ለአጥር እና የወንዝ መከላከያ ስራ በሆቴሉ ዲዛይን ውስጥ ያልተካተተ መሆኑን ግንዛቤ ተይዟል፡፡ ስለሆነም በሆቴሉ ዲዛይን ውስጥ ላልተካተተ ስራ በቀረጥ ነጻ የገባውን ብረት ስራ ላይ እንዲውል መፍቀድ ተገቢ ባለመሆኑ ቅሬታ አቅራቢው በትርፍነት በተገኙ ላይ ቀረጥና ታክሱን ቅጣት ሳይታከልበት መክፈል እንደሚያስፈልግ ታምኖበታል፡፡ በመሆኑም ዳይሬክቶሬቱ ባደረገው ማጣራት ተራፊው ብረት ለሶስተኛ ወገን ያልተላለፈ እና በግንባታው ቅጥር ግቢ ውስጥ የሚገኝ በመሆኑ በትርፍነት በተገኘው 89,620 ኪ.ግ አርማታ ብረት ላይ ቀረጥና ታክስ ከፍለው እንዲስተናገዱ ተወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ ቅር የተሰኘ ማንኛውም ሰው በአዋጁ አንቀጽ 155 መሠረት ለታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ቅሬታ ማቅረብ ይችላል። ጽ/ቤቱም ለተገቢው አፈጻጸም የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ተመዝግቦለታል።

ከሠላምታ ጋር

ዘመኑ ዘገዬ
Zemenu Zegeye
Customs Complaint Review Directorate Director

ግልባጭ፣

- ለአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

አዲስ አበባ

መ.ቁ 3526